ታህሳስ ፲ ቀን ፳፻ ዓ.ም(Dec 20, 2007)

# ዝክረ ሣሙዔል-2ኛ ሙት ዓመት መታሰቢያ!

ውድ ሣሙዔል ሆይ! እንዴት ባጀህ ? ጃል!

አምላክ የተመሰገን ይሁን እኛ በእጅጉ ደህና ነን፣ እግዚአብሔር ይመስገን። ይኸውና አንተ ከተለየኸን 2 ድፍን ዓመት ሊሞላ የሳምንት ቀናቶች ቀሩ። አቤት! የጊዜው መሮጥ? ሆኖም ግን እንኳን ሁለት ዓመት ሣምንትም ያደረግን አልመሰለን። በሕይወት ብትለየንም ሁሌ በልባችን ውስጥ አለህ አትጠፋም ብዬህ አለነበረም። አሁን ደግሞ በዚህ ሰሞን በዲሴንበር 8 /2007 (የፈረንጆች አቆጣ) ”የደብተራው ድረ-ገጽና የደብተራው ቀን ”በሚል (እግዚአብሔር የኃሳባቸውን ይሙላላቸውና) 2ኛ ዓመትን ለማስታወስ የእናንተና የእነ ደብተራው ተከታዮች ባዘጋጁልን ግብዣ ላይ ተሰባስበን ተግኝተን ደብተራውንና ደብተራዎችን ስናነሳ፤ የደብተራዎችንም ገድል አብረን ስንዘክር አደርን። ተመስገን! ይህንንስ ማን ክፉ ብሎት።

ሣሙዔል! ሌላም ነገር አለኝ ላጫውትህ። ይኸው በዚሁ ዓመትም ውስጥ አንድ የተማሩና የተመራመሩ የኢትዮጵያ አባትና ሊቅ አለቃ አያሌው ታምሩ፣ አንተ ወደ አለህበት፣ ወደ ተከበረውና ፀጋ ወደ ተሞላበት ዓለም ዘለቁ። አቤት የአምላክ ሥራ! የራሱን ሰዎች ያውቃልና እሳችውንም እንዳማረባቸው በወግ በማእረግ ጠራቸው። በሰዎች ክፋትና ኃጥያት ምክንያት በምትናጠው የምድር ዓለም ላይ ኢትዮጵያም አብራ መንገላታቷ አለቀርምና፣ በዚሁ የኃጥያተኞች ተግባር ኢትዮጵያም ተወጣጥራ በምትናጥበት ጊዜ፣ የኢትዮጵያው ሊቅ አባት አለቃ አያሌው ታምሩ፣ የኢትዮጵያን ታሪክ በማስተማር፣ ባህሏን በመዘከር፣ ተተኪው ትውልድ ሀገሩንና የሀገር አንድነቱን እንዴት ጠብቆ ማቆየት እንዳለበት፣ በስነ-ጽሁፋቸውና በቅኔ ችሎታቸው ሲታደጉ፣ ኖረዋል። እርግጥ ነው ሰዎች ነንና እኛ ከእኛ በመለየታቸው ብናዝንም ከእኛ ደግሞ የፈጣሪ ይበልጣልና ባሰበውና በፈቀደው ቀን (ያችን ቀን ማምለጥ አይቻልምና) የእድሜ ጸጋውን እንደሰጣቸው ሁሉ በፈቃዱ ደግሞ መንገዱንም አመቻችቶ፣ ና ብሎ ጠራቸው። ከዚህ በፊት እንደፃፍኩልህ እንዲህ ዓይነቱን እድል የሚገኙት ጥቂቶች ናቸው።

ውድ ሣሙዔል! በዓለፈው ዓመት የመጀመሪያ ደብዳበዬን እዚህ የክፋትና የኃጥያተኞች መናኸሪያ ከሆነችው ምድር ላይ ሆኘ ወደ አንተ ደብደቤዬን ስልክ፣ ወደ እርሱ ወደ ሄድክበት ዓለም የዘለቁትን፣ ለአንተና ለመሰሎችህ ምሳሌ የሆኗችሁን የቀድሞ የኢትዮጵያ ዓርበኞችንና፣ ኢትዮጵያ በባእዳን እንዳትገዛ፣ እንዳትረክስ መሬቷን ጭምር አውግዘውና ገዝተው መስዋእት የሆኑትን ዓቡን(ጴጥሮስን) አግኝተህ ይሆን? ብዬ መጠየቄን አትዘነጋውም። አሁንም በቅርቡ ከ 3 ዓመት በፊት (ትናንትና ተወለደው) መብታችንና ድምፃችን አይሰረቅብን ብለው በመጠየቃቸው የተቀጠፉት እንቦቃቅላ ወጣቶች፣ ህፃናት ወንዶች፣ ሴቶች፣ ሕፃናት ተጫውተውና ሮጠው ሳይጠግቡ ይሄ ሁሉ መዓት የወረደባቸው ለምን ይሆን? ብዬ እንደጠየኩህ ሁሉ አንተ ጋ ካለው ፈጣሪያቸው ጋር ይሄንን ሁሉ መዓት አጫውተውት ይሆን እንዳልኩህ ታስታውሳለህ። አሁን ደግሞ ”ክርስቶስ ለሥጋው አደላ እንደሚባለው” ሆኖ ነው መሰል ለኢትዮጵያ ቀናና ደግ ሲያስቡ የኖሩትን አባት አለቃ አያሌው ታምሩን ወደ እርሱ ፀጋ ወደ ተሞላበትና ወደ ተከበረው ዓለም ተጠርተው መጥተዋልና ሳታገኛቸው አትቀርም ብዬ ነው ዛሬም ጥያቄን ላዥጎድጉድ የቸኮልኩት። ሣሙዔል! እስቲ እንዲያው በሞቴ ስለ ላይኛው ቤት ልጠይቅህ ምን ምን እያነሳችሁ

እንደምትጫወቱ። ሊቁ አለቃ አያሌው ታምሩስ ኢትዮጵያ ላይ የወረደውን መዓት፣ በቤት-ክርስቲያናትና በቤተ መቅደሶች፣ እንዲሁም በምእመናኖቿ ላይ የዓምላክን ስም እየጠሩ ሰይጣናዊ ተግባር የሚከናውኑትንና ቤተ-ክርስቲያኖን ያረክሱና እያረከሱ ያሉትን ዲያቢሎሶች፣ ከፈጣሪ ጋር ተገናኝተው ተጫውተውት ይሆን? ሣሙዔል! እርግጥ ነው አውቃለሁ ዓምላክ እንደኛ አይደለም፤ አይቸኩልምም። ቢሆንም ግን እንዲህ ዓይነት ጉግማንጉጎች፣ ሰው የተባለው ፍጡር የመገኛውና የእነ ድንቅነሽ መፍለቂያ አድርጎ የፈጠራትን ሀገር(ኢትዮጵያን)፣ እንዲህ ሲያስጨንቋዋትና የምድር ሲኦል ሲያደርጓዋት ግን የእርሱ ዝምታና ትዕግስት ቢበዛብኝ ነው መጠየቄ። አዎ! ጥቂት ግብዞች፣ መርገምቶች በሚፈጽሙት ተግባርና በራሳችን ምክንያት እነሆ እስረኛ ሆነን። አዎ! ጥቂት ግብዞች በሚሰሩት ተንኮልና የክፋት ሥራ ብዙሃኑ ለኃጢዓት ተዳረገ። እርግጥ እነኝህ የክፋት ሰዎች ደግመው ደጋግመው ፈጣሪን አሣዝነውት ይሆናል። ግን በጥቂቶች ኃጢዓትና ተግባር ብዙሀኑ እስከመቼ ነው እየተቀጣ የሚኖረው ብለህ ጠይቅልኝ እባክህ? አውቃለሁ የእሱ ሚዛን የማይዛባ ነውና አንድ በለን በልልኝ። ይሄንን ግፍና በደል ሁሉ አያይም፣ አይሰማም ለማለት አልደፍርም፤ ግን ከልክ በላይ ያለፈ መሆኑን ግን አስታውሰልን። እኛን ከእርሱ ከፈጣሪ ጋር የሚያቀያይሙን በኃጢዓት የተበከሉ አህዛቦች በሚሰሩት ተግባር ነውና ይህንንም አትዘንጋው በልልኝ። አባታችን ጌታ ሆይ! ምነዋ! ጥቂት ግብዞችና መርገምቶች በሰሩት ኃጢዓት ብዙሃኑ እንዳይጎዳብኝ ብለህ አይደል እንዴ ለዓለም መድህን ለመሆን አንተስ ተሰቃይተህ የተሰቀልከው? ብለህ ጠይቅልኝ። ደግሞም እኛ በኃጢያት የተሞላች ዓለም ላይ መኖራችንን አትርሳ? በልና ጠይቅልኝ አደራ።

ሣሙዔል! ይሄን ሁሉ የማነሣልህ አንተ ጋ ያለው ፈጣሪያችን እኛን እንዳልዘነጋን የምታውቀው ምስጢር ካለ፣ ሹክ እንድትለኝ ጓጉቼ ነው። የነብዮ መሐመድን ቃል ተቀባዮች፣ የእሥልምና ኃይማኖት አማኞችና የክርስቲያን ኃይማኖት እምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያዊያኖች፣ በአንድ ላይ ለረዥም ዘመናት አብረው በመኖር ተዋልደውና ተፋቅረው የኖሩባት፣ የምሳሌ አገር ያደረጋትን ኢትዮጵያ፣ ያስታውሳት ዘንድ ብዬ ብጨነቅ ነው ጭንቀቴን አካፍዬህ የኛንም ጭንቀት ለአንድዬ እንድታድርስ የምነግርህ። አበዛሁብህ መሰለኝ! ግን በዓመት አንዴ ነውና የምጽፍልህ የዓመቱን ጣጣ ዘርዝሬ ልንገርህ ብዬ ነው። እንዲህም እኮ ይባላል ሣሚ። ነብዩ መሐመድ የሠላምና የፍቅር ሃገር ናት፣ ”ወደ ሃበሻ አገር ተሰደዱ፣ እዚያ ስትደርሱም ጥሩ አድርገው ይቀበሏችኋል” ብለው መሐመድ የመሰከሩላትን ኢትዮጵያ፣ እንዲህ መከራዋና ፍዳዋ ከልክ አልፎ፣ ልቅሶዋን ወደ ፈጣሪዋ እያሰማች እያለ፣ ችልታው ለምን ይሆን ብዬ ነው። ሣሙዔል! እርግጥ ነው መቼስ እኛ እዚህ ያለነው አሁንም ፈጣሪን ማሳዘናችን አይቀርምና የኛን ሣይሆን የርሱን ይቅር ባይነት እናውቃለንና እዚያ እርሱ ጋ ያላችሁት በሙሉ ስትገናኙ የሚበጀውን ምከሩና የምትመክሩትንም ለእኛ ግለጡልን አደራ። ይህንን የምለው ደግመን ፈጣሪን እንዳናሳዝነው ይጠቅመናልና ነው። አለቃ አያሌውም ቢሆኑ አሁን ነውና ወደ እናንተ የዘለቁት እዚህ ስለሚሆነውና ስለሚደረገው ጉድ ያጫውቱኃል።

በል እንግዲህ ጨዋታዬን እዚህ ላቁምና እኔም እንደ አንተ ተራው ደርሶኝ ወደ እርሱ ወደተከበረው ዓለም እስክመጣ ድረስ ፈጣሪ ነፍስህ በገነት ያሳርፍልን እያልኩ እስከሚቀጥለው ደብዳበዬ እሰናበትሃለሁ።
የአንተዋ አያልነሽ ነኝ

ታሕሳስ ፲ ቀን ፳፻ ዓ.ም